# የፍትህ (ጀስቲስ) ዲፓርትመንት) በኮሎራዶ አስተዳደር ፍርድ ቤት ስርዓት ውስጥ የነበሩ የቋንቋ መሰናክሎች በተመለከተ የነበረው ምርመራ በስምምነት ፈታ

ዋሺንግተን - የፍትህ ዲፓርትመንት፣ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው (ኤል.ኢ.ፒ.) ሰዎች በፍርድ ቤቱ ስርዓት ወቅታዊና ብቃት ያለው የቋንቋ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያደርግ የመፍትሄ ስምምነት ላይ ከኮሎራዶ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ጽ/ቤት (ኦ.ኤ.ሲ.ኦ.ኤ.ሲ.) ጋር መድረሱን ዛሬ አስታውቋል።

ኦ.ኤ.ሲ.፣ የሰራተኞችን የካሳ የይገባኛል ጥያቄዎች፣ እንዲሁም ደግሞ እንደ የፍትሐብሔር መብቶች፣ የአካባቢ ፍትህ፣ ትምህርትና መጓጓዣ በመሳሰሉ ሌሎች ወሳኝ ዘርፎች የሚነሱ የይገባኛል ጥያቄዎችን የሚሰማ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ነው። ስምምነቱ በ1964 በወጣው የፍትሐብሔር መብቶች ሕግ ርዕስ (ታይትል) VI መሠረት የፍትህ ዲፓርትመንት በኦ.ኤ.ሲ. ያደርገው የነበረ ምርመራን ይፈታል። ርዕስ VI፣ እንደ ኦ.ኤ.ሲ. ባሉ የፌዴራል ዕርዳታ ተቀባዮች በዘር ፣ በቀለም ፣ እና በብሔራዊ መነሻ (ናሽናል ኦሪጂን) መሠረት መድልዎን ይከለክላል። ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች በፍርድ ቤት ችሎታቸው እንዲገነዘቡና እንዲሳተፉ የሚያግዝ ብቁ አስተርጓሚዎችን እንዳይሰጥ የሚከለክል ደንብን ጨምሮ በኦ.ኤ.ሲ. ርዕስ VI የሚያዘውን በመተግበር ዘንድ ስጋቶች እንዳሉ የፍትህ ዲፓርትመንቱ ባደረገው ምርመራ በግላጭ አሳይቷል።

“ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው ሰዎች በፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ የሚያስችል የሚፈልጉትን የቋንቋ አገልግሎቶች አለማግኘት በእውነቱ አስከፊ መዘዞች ያስከትላል። በፍትህ ስርዓታችን ውስጥ ያሉትን የቋንቋ መሰናክሎችን ሳናፈርስ 'ፍትህ ለሁሉም' ተደራሽ መሆን አለበት በማለት አገራችን የገባችው ቃል ማሳካት አንችልም” በማለት የፍትሐብሔር መብቶች ዲቪዥን ዋና ምክትል ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ህግ (ፕሪንሲፓል ደፒዩቲ አሲስታንት አተርኒ ጀነራል) የሆኑት ፓሜላ ኤስ. ካላን ተናግረዋል። “የ ኦ.ኤ.ሲ. ዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) እና አመራር ይህንን የተገባው ቃልን ለመፈፀም እርምጃ በመውሰዳቸውና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው የፍርድ ቤት ተጠቃሚዎች ወሳኝ አገልግሎቶችን ለመስጠት ላሳዩት ቁርጠኝነት አመሰግናለሁ።” በማለትም አክለዋል።

“ይህ ስምምነት በኮሎራዶው የአስተዳደር ፍርድ ቤት ስርዓት ውስጥ ፍትህን ለሚሹ፣ ነገር ግን እንግሊዝኛ ለማይናገሩ፣ ሰዎች እውነተኛ እገዛን ይሰጣል” ብለዋል የኮሎራዶ ዲስትሪክት ተጠባባቂ የዩናይትድ ስቴትስ ጠበቃ ማት ኪርስች። “የኮሎራዶ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ጽ/ቤት ከእኛ ቢሮና ከፍትሐብሔር መብቶች ዲቪዥን ጋር በመሆን ከእንግሊዝኛ ውጭ ሌሎች ቋንቋዎችን የሚናገሩ ኮሎራዶ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦችን የሚጠቅም ስምምነት በመፍጠር ላይ አብሮ የመስራት እድል እንዳለ መገንዘቡን አደንቃለሁ።” በማለትም አክለዋል።

የኦ.ኤ.ሲ. የማስፈጸሚያ አተገባበር ቁልፍ ገጽታ ደንብ (ሩል) 21 መከለስ ይሆናል፣ ይህም በአሁን ሰአት ኦ.ኤ.ሲ. በፍርድ ቤት ሂደቶች ውሱን እንግሊዝኛ ችሎታ ላላቸው ግለሰቦችን ያለምንም ወጪ ብቁ አስተርጓሚዎችን እንዲያቀርብ ያስገድዳል። በተጨማሪም፣ ኦ.ኤ.ሲ. የቋንቋ ተደራሽነት ፖሊሲና ዕቅድ

በመፍጠር ቢያንስ በብዛት ከሚያጋጥሟቸው በስምንቱ ቋንቋዎች የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶችን እንደሚሰጡ ማስታወቂያ ለማድረግ ተስማምቷል። ኦ.ኤ.ሲ. የቋንቋ ተደራሽነት ቅሬታ ሂደትን በመፍጠር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣ እንዲሁም ለዳኞች ፣ ለሠራተኞችና ለሥራ ተቋራጮች በኤል.ኢ.ፒ. ጉዳዮች ላይ ዓመታዊ ሥልጠና እንዲሰጥ ያስገድዳል። ለዚህ ጉዳይ ፈጣንና የትብብር መፍትሄ በመስጠት ረገድ የኦ.ኤ.ሲ. ዋና ዳኛና የኮሎራዶ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ጠንካራ ድጋፍና ንቁ ተሳትፎ ቁልፍ ነበሩ።

ዛሬ በተፈረመው ስምምነት ዝርዝር ነጥቦች መሠረት የፍትህ ዲፓርትመንት፣ ኦ.ኤ.ሲ. ቃል በገባው መሰረት ተግባር ላይ ማዋሉን ለሁለት ዓመታት ያህል ይቆጣጠረዋል።

የ1964ቱ የፍትሐብሔር መብቶች ሕግ ርዕስ VI ተፈጻሚነትን የፍትሐብሔር መብቶች ዲቪዥን ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የፍትሐብሔር መብቶች ዲቪዥን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በድረገጹ www.justice.gov/crt ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታና ርዕስ VI በተመለከተ መረጃ በ www.lep.gov ይገኛል። የማህበረሰቡ አባላት ሊከሰቱ ለሚችሉ የፍትሐብሔር መብቶች ጥሰቶችን በ https://civilrights.justice.gov/report/ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

# # #